OFFICE OF THE STATE
SUPERINTENDENT OF EDUCATION

ውድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ፣

በጸደይ 2023፣ የእርሶ ልጅ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት (ELA)/የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ እና በሂሳብ ላይ የበርካታ-ስቴት አማራጭ ምዘና (መልቲ-ስቴት አልተርኔት አሴስመንት) (MSAA) ወስዶ/ወስዳ ነበር። MSAA ከፍ ያለ የማገናዘብ ጉድለቶች ላሏቸው ተማሪዎች ሰፋ ላለ የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ውጤት ለማዘጋጀት፣ ከፍተኛ የአካዳሚክ ውጤቶች ጭማሪ ለማበረታታት የታቀደ የተቀናጀ የምዘና ሲስተም ነው።

ከ3-8 እና 11ኛ ክፍሎች ውስጥ ላሉ ለአማራጭ ምዘናው ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች በELA/የማንበብ እና የመጻፍ ችሎታ እና ሂሳብ MSAA አስፈላጊ ነው። MSAS ተማሪዎች በነጻነት ምላሽ እንዲሰጡ የሚረዳ አብሮ የተገጠመለት በዋናኘነት ኦንላይን የሚተዳደር ነው። በተማሪዎቹ የግል ፍላጎቶች መሰረት በማድረግ፣ የተወሰኑ ተማሪዎች ከኮምፒውተሩ ጋር በቀጥታ ግንኙነት የሚኖራቸው ሲሆን ሌሎች ደግሞ በፈተና አስተዳዳሪ በተዘጋጀ የጽሁፍ ሰነዶች አማካኝነት ግንኙነት ይኖራቸዋል።

በዚህ ውስጥ የተጠቀለለው መምሪያ ከልጅዎ የMSAA ውጤት ሪፖርት ሊማሯቸው የሚችሉትን አስፈላጊ ነጥቦችን ያሳይዎታል። በተጨማሪ ልጅዎ በመጪው አመት እንዲያሻሽል እንዲረዳው ግብአቶችን ያቀርብሎታል። የልጅዎ የውጤት ሪፖርቶች ካልደረሱዎት፣ እባክዎ ልጅዎ በ2022-23 የተማረበትን/ችበትን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ እና ለቅጂው
ይጠይቁ።

የምዘና ውጤቶች የልጅዎን አጠቃላይ የትምህርት ታሪክ እንደማይናገሩ እናውቃለን። ውጤቶቹ ከበርካታ መለኪያዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን
– በጠቅላላው የልጅዎን የትምህርት ቤት እድገት ሙሉ ምስል የሚፈጥሩ የዘገባ ካርድ ውጤቶችን፣ የክፍል ውስጥ አፈፃፀምን እና የአስተማሪ ግብረመልስን ይጨምራሉ። በዚያ ምስል ውስጥ፣ አመታዊ ምዘናዎቹ እርስዎ እና የልጅዎ አስተማሪዎች የእርስዎ ልጅ ባለፈው አመት ለELA እና ሂሳብ የመንግስት የይዘት መስፈርቶች ልጅዎ ያሳየውን እድገት በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ የተሰሩ ናቸው። እንዲሁም ትምህርት ቤቶች ሁሉንም ተማሪዎች ለመደገፍ ምን ዓይነት ቁሳቁሶች እንደሚፈልጉ በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ግምገማዎች ይረዱናል።

በመጨረሻ፣ የኛ እቅድ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ስኬታማ ለመሆን እና ህልሞቻቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን ለማሳካት መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ነው። እርስዎ ስለምዘናዎች አጠቃላይ ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎ የእኛን ድህረገጽ በ osse.dc.gov/service/alternate-assessments ይጎብኙ ወይም ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ይወያዩ። ስለ ምዘናው የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት እና የናሙና እቃዎችን ለማግኘት በዚህ መመሪያ ገጽ 4 ላይ ያሉትን መገልገያዎች መጠቀም ይችላሉ።

በስቴት ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSSE) ውስጥ፣ በሁሉም ተማሪዎች እምቅ ችሎታ እናምናለን፣ እና ሁሉም ተማሪዎች መማር እንደሚችሉ እና ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊደርሱ እንደሚችሉ እናምናለን። ልጅዎ እንዲሳካለት ከእርስዎ ጋር አጋር ሆነን መስራቱን እናደንቃለን።


እናመሰግናለን፣

ዶ/ር Christina Grant
የDC ግዛት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ

1050 First Street NE, Washington, DC 20002
(202) 727-6436 TTY: 711 | osse.dc.gov

# የውጤት ዘገባው ሲብራራ፡- ፊት

ይህ መመሪያ ከልጅዎ የውጤት ሪፖርት ሊማሯቸው ወደሚችሏቸው በጣም አስፈላጊ የግንዛቤ ነጥቦች ይመራዎታል። እንዲሁም ልጅዎ በሚመጣው አመት አፈፃፀሙን እንዲያሻሽል ለመርዳት አጋዥ ግብዓቶችን ይሰጥዎታል።



ሚስጥራዊ ይዘት

ስም፡- ስኮት ቴስትቴከር
መታወቂያ ቁጥር፡ 0123456789
ትምህርት ቤት፡ Anywhere Middle School
የፈተና ቀን፡ ጸደይ 2022
ክፍል፡ 06

**በሪፖርቱ ውስጥ ምን አለ?**

**ገጽ 1:** በዚህ ዓመት ፈተና ላይ የልጅዎ አፈጻጸም የማጠቃለያ ሀሳብን ይዟል።
**ገጽ 2:** ከMSAA የተጻፈ የመግቢያ ደብዳቤ እና ልጅዎን ለመደገፍ ቀጣይ እርምጃዎችን ይዟል።

1

**የአፈጻጸም የማጠቃለያ ሀሳብ**

በእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት እና ሂሳብ የስኮት አፈጻጸም ከታች ተገልጿል።

**የእንግሊዘኛ ቋንቋ አርትስ**

| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |
|---|---|---|---|
| 1200-1230 | 1231-1236 | 1237-1250 | 1251-1290 |

የአፈፃፀም ደረጃ: **ደረጃ 3**
ውጤ: **1245**

1245

የሚጠበቁ ነገሮችን ያሟላል

የተማሪ የፈተና ውጤት ሊለያይ ይችላል። ልጅዎ እንደገና የሚፈተኑ ከሆነ፣ ከ1243 እና 1247 መካከል የሆነ ውጤት የማግኘት እድል ያላቸው ይመስላል።

የእንግሊዝኛ ቋንቋ አርት ንባብ እና መጻፍ አለው። በእያንዳንዱ ዘርፍ ሊገኙ የሚችሉ የነጥቦች መቶኛን ከታች ይመልከቱ።

በንባብ 66% በመጻፍ 80%

**ሂሳብ**

| ደረጃ 1 | ደረጃ 2 | ደረጃ 3 | ደረጃ 4 |
|---|---|---|---|
| 1200-1232 | 1233-1238 | 1239-1250 | 1251-1290 |

የአፈፃፀም ደረጃ: **ደረጃ 3**
ውጤ: **1244**

1244

የሚጠበቁ ነገሮችን ያሟላል

የተማሪ የፈተና ውጤት ሊለያይ ይችላል። ልጅዎ እንደገና የሚፈተኑ ከሆነ፣ ከ1241 እና 1247 መካከል የሆነ ውጤት የማግኘት እድል ያላቸው ይመስላል።

**የአፈፃፀም ደረጃ ገላጮች**

2

ከላይ ላለው ለእያንዳንዱ የይዘት ዘርፍ የውጤት መለኪያ ደረጃ እና የአፈፃፀም ደረጃ፣ በእንግሊዝኛ ቋንቋ አርትስ (ELA) እና በሂሳብ ፈተናዎች ላይ የ ስኮት'ን አፈጻጸም ያጠቃልላል። ከታች ያሉት የአፈፃፀም ደረጃ ገላጮች የዚህ ደረጃ አፈጻጸም ያላቸው ልጆች በአጠቃላይ የሚያሳዩትን እውቀት እና ክህሎቶችን ይገልጻሉ።

**የእንግሊዘኛ ቋንቋ አርትስ**

ጽሁፉ ምን እንደሚለው የሚመለከቱትን ጥያቄዎች ለመመለስ፣ ስለ ባህሪያት ግምቶችን የሚደግፉ የጽሁፍ ዝርዝሮችን ለመለየት፣ እና ጽሁፍ ለማጠቃለል የሥነ-ጽሁፍ ጽሁፎችን ከግልጽ እስከ ተዘዋዋሪ ሀሳቦች ጋር መጠቀም
ቁልፍ ሀሳቦችን የሚያሳድጉ ዝርዝሮችን ለመለየት፣ የጸሐፊውን ሀሳብ በማስረጃ ለመደገፍ፣ እና ከተለያዩ ጽሁፎች መረጃን ለማጠቃለል የመረጃ ጽሁፎችን ከግልጽ እስከ ተዘዋዋሪ ሀሳቦች ጋር መጠቀም
በርካታ የትርጉም ያላቸው ቃላትን ለመተርጎም አውድ መጠቀም
በዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ ለተጠራ-ልዩ የሆኑ ቃላትን መጠቀም
የክስተቶች ቅደም ተከተልን ለማስተላለፍ ቀጣይ ዝግጅትን ለመለየት እና የመሸጋገሪያ ቃላትን እና ሀረጎች (እንደ በኋላ ወይም ከሁሉም በማስቀደም ዓይነት) በመጠቀም አፈ-ታሪክን ማዘጋጀት
መግቢያ፣ አካል፣ እና ማጠቃለያን በመለየት መረጃ የሚያቀርብ የማብራሪያ ጽሁፍ ማዘጋጀት
በቅንጅት የከፊል ትዕዛዝ፣ ሀሳብ ማሳደግ እና/ወይም የሀሳብ ስብስቦችን የያዘ የማብራሪያ ጽሁፍ መጻፍ

**ሂሳብ**

የቁጥር መስመር ላይ የፖዘቲቭ እና የኔገቲቭ ዋጋዎች ግንዛቤን ማሳየት
የውሂብ ስብስብ ውስጥ አማካይ፣ ሚዲያን (መካከለኛ) ወይም ሞድ (ሁነታ) መግለጽ
በሙሉ ቁጥሮች ወይም አስርዮች ጥያቄዎችን መስራት፣ የሂሳብ ቋንቋ እና የምልክት ውክልናዎችን በመጠቀም (ለምሳሌ፣ <፣ >፣ =)
የቃል ጥያቄዎችን በመቶኛ፣ ሬሾ፣ ሬት (መጠን)፣ ወይም በተለዋዋጭ (ቫሪየብል) መስራት
የ ፓራሌሎግራም ስፋትን መስላት

© 2022 MSAA. ሁሉም መብቶች በሕግ


**1) የአፈፃፀም ደረጃዎች** የልጅዎ ውጤት ከአራቱ የአፈፃፀም ደረጃዎች ውስጥ በአንዱ ይመደባል። የአፈፃፀም ደረጃዎቹ ልጅዎ በክፍል ደረጃ የሚጠበቅበትን/የሚጠበቅባትን አሟልቶ/ታ እንደሆነ ይለያሉ። በ ደረጃ 3 ወይም 4 ላይ ያለው ነጥብ ልጅዎ በርዕሰ ጉዳዩ የሚጠበቅበትን/ባትን አሟልቷል/ታለች ወይም አልፏል/አልፋለች ማለት ነው። ከደረጃ 3 በታች የሚያስመዘግቡ ተማሪዎች አሁንም በክፍል ደረጃ ክህሎቶች እና እውቀት እያዳበሩ ሊሆን ይችላል።

**2) የአፈፃፀም ደረጃ ገላጮች** ይህ ክፍል የልጅዎ ደረጃ አካባቢ አፈጻጸም ያላቸው ተማሪዎች በአጠቃላይ የሚታይ እውቀት እና ክህሎቶችን ይገልጻል።

# የውጤት ዘገባው ሲብራራ፡- ይመለሱ

**3) የምዘናው አጠቃላይ እይታ** ይህ ክፍል MSAA እና የሚወስዱትን ተማሪዎች ፍላጎቶችን እንዴት እንደሚደግፍ ላይ የኋላ ታሪክ መረጃ አለው።



ውድ ወላጆች እና አሳዳጊዎች፣

ይህ ሪፖርት የ 2022 የኦንላይን የበርካታ-ስቴት አማራጭ ምዘና (MSAA) ላይ የልጅዎን አፈጻጸም ያጠቃልላል። ይህ ሪፖርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ አርትስ (ELA)፣ ሂሳብ፣ እና ሳይንስ የውጤት መለኪያ ደረጃ እና የአፈጻጸም ደረጃዎችን ያሳያል። እንዲሁም በንባብ እና በመጻፍ ሊገኙ የቻሉ ነጥቦች ከመቶ ተገልጿል። የአፈፃፀም ደረጃ ገላጮች የዚህ ደረጃ አፈጻጸም ያላቸው ልጆች በአጠቃላይ የሚያሳዩትን እውቀት እና ክህሎቶችን ይገልጻሉ።

MSAA ከ 3-8 እና 11 ክፍሎች ውስጥ ያሉ እና ጉልህ የአዕምሮ ማሰብ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ተማሪዎችን ለመመዘን የተነደፈ ነው እና ከእርስዎ ስቴት የይዘት ደረጃዎች ጋር የሚሄድ እና ከእርሱ የተቀዳ የአካዳሚክ ይዘትን ይለካል። ፈተናው ተማሪዎች በጣም በሚያውቋቸው የትምህርት ጽሁፎች ፈተና እንዲወስዱ እና የሚያውቁትን ነገር እና ማድረግ የሚችሉትን ነገር እንዲነጋገሩ የሚያስችሉ በርካታ በውስጥ-የተገነቡ ድጋፎችን ይይዛል። እንዚህ በ MSAA ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ በውስጥ-የተገነቡ ድጋፎች ናቸው፥

- አጠር ያሉ የ ELA የንባብ አንቀጾች
- ተማሪዎች የንባብ አንቀጹን እንዲገነዘቡ የሚረዷቸው ምስሎች፣ ቻርቶች፣ ሰንጠረዦች፣ እና ካርታዎች
- አስፈላጊ ሀሳቦችን እና ጽንሰ-ሀሳቦችን የሚያብራሩ ሞዴሎች እና ምሳሌዎች
- በሂሳብ ፈተናዎች ላይ ትናንሽ ቁጥሮች

በሚቻለው ትልቁ መጠን የመግባቢያ ራስ-መቻልን ለመደገፍ፣ MSAA ከተለያዩ የመግባቢያ ሞዴሎች እና ስርዓቶች ጋር እንዲሰራ የተነደፈ ነው። እባክዎ ልጅዎ በ MSAA ላይ የተጠቀማቸውን ድጋፎች ከልጅዎ መምህር ጋር ተወያዩ።

ልጅዎን ለመርዳት ተጨማሪ መረጃ እና ግብዓቶች የእርስዎ ስቴት አማራጭ ምዘና ድረገጽ ላይ ወይም የልጅዎን መምህር በማነጋገር ይገኛሉ። ይህን ደብዳቤ ወይም የልጅዎን ሪፖርት በሌላ ቅርጸት ከፈለጉ፣ እባክዎ የእርስዎ ስቴት የትምህርት መምሪያን ያነጋግሩ።

**ቀጣይ ምን ዓይነት ክህሎቶች ላይ መስራት ይቻላል?**

**የእንግሊዘኛ ቋንቋ አርትስ**

+ ማጠቃለያን ለመደገፍ ዝርዝሮችን መጠቀም
+ በግለሰቦች፣ ኩነቶች ወይም ሀሳቦች መካከል ያሉ ግንኙነቶች አንዱ ሌላው ላይ እንዴት ተጽእኖ እንደሚያመጡ ለማብራራት ማስረጃ መጠቀም
+ ሁለት የተለያዩ ጸሀፊዎች በአንድ ርእስ ላይ የጻፉትን ጽሁፍ ማነጻጸር
+ የሀረጎች ትርጉምን ለመለየት አውድ መጠቀም
+ ማጠቃለያን ያካተተ የጽሁፍ ምርትን መፍጠር

**ሂሳብ**

+ የሂሳብ ቃላትን እና ምልክቶችን መጠቀም (<፣ >፣ =)
+ የማባዛት እና የማካፈል ጥያቄዎችን በአዎንታዊ/አሉታዊ ቁጥሮች መስራት
+ ከመቶኛ፣ መጠኖች፣ እና ሬሾዎች ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን መስራት
+ የክብ ዙሪያ እና ስፋትን መለየት
+ የ ባለሶስት አቅጣጫ ምስል የገጽታ ስፋትን መለየት
+ ተለዋዋጭ መግለጫዎችን መገምገም
+ ውሂብን በባር ግራፍ እና በሰንጠረዦች ማነጻጸር

**አሁን ምን ይደረጋል?**

ይህን ሪፖርት ከ ስኮት አስተማሪዎች ጋር በሚኖርዎት ቀጣይ ውይይት ላይ ይዘው ይምጡ።
የስኮትን መምህራኖች የሚከተሉትን መጠየቅ ይችላሉ፣

- በዚህ ዓመት ELA እና ሂሳብ ላይ የ ስኮት መማር ምን ይመስላል?
- ስኮት እንዴት እየሰራ ነው?
- በዚህ ዓመት ከስኮት ጋር አብሬ ለመስራት እንዴት ይሄን መረጃ እጠቀማለሁ?
- ስኮትን ለመደገፍ የትኞዎቹን ግብአቶች መጠቀም አለብኝ?

© 2022 MSAA. ሁሉም መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው።


**4) ቀጣይ ምን ዓይነት ክህሎቶች ላይ መስራት ይቻላል?** ይህ ክፍል ልጅዎ በአፈጻጸማቸው መሰረት ቀጣይ እንዲሰሩባቸው የተጠቆሙ ክህሎቶችን ያካትታል።

**5) አሁን ምን ይደረጋል?** በውጤት ሪፖርቱ ላይ ያለው መረጃ የተማሪውን እድገት ለመለካት እና የክህሎት ማዳበሪያ መምሪያን ለመስጠት የታለመ ነው። ይህ ክፍል የልጅዎን አስተማሪ ስለ ልጅዎ አፈጻጸም ሊጠይቋቸው የሚችሉ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ያቀርባል።

## ግብአቶች እና ድጋፍ

ከዚህ በታች የእርስዎ ልጅ አፈፃፀሙን እንዲያሳድግ የሚያግዙ፣ እንዲሁም ውጤቱን ከልጅዎ እና ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ለመወያየት ጠቃሚ ምክሮች የሚሰጡ በርካታ አጋዥ ግብአቶች አሉ።

### ስለ MSAA የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ?

ስለ MSAA የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሚከተሉትን ድህረገጾች ይጎብኙ ፥

- OSSE.dc.gov/service/alternate-assessments forstatewideassessmentresults
- msaastates.com ለinformationontheassessmentandresourcesforfamiliesand educators
- msaaassessment.org/sample-items ለ ናሙና እቃዎች እና የውጤት ሩቢክስ

### ከልጅዎ ጋር ስለ ውጤቱ ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

እንክብካቤ ሰጪዎች ከልጆቻቸው ጋር መነጋገር ላይ ባለሙያዎች ናቸው። ስለልጅዎ የፈተና ውጤት ሲናገሩ ማስታወስ ያለብዎት ጥቂት ጠቃሚ ነገሮች ከዚህ በታች አሉ፦

- የፈተና ውጤቶች አንድ የአፈፃፀም መለኪያ ብቻ ናቸው።
- ጥንካሬዎች ላይ አተኩሩ።
- የዕድገት ዘርፎችን (ለምሳሌ፣ የኦንላይን ላይ ልምምድ፣ ከአስተማሪ ጋር መስራት) ለማስተናገድ የሚያግዙ ስልቶችን ተወያዩ።

### ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ስለ ውጤቱ ለመነጋገር ይፈልጋሉ?

ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ውይይትን ለመምራት የሚረዱ ጥቂት ጥያቄዎች ከዚህ በታች አሉ፦

- በዚህ አመት የልጄ የሂሳብ የመማር ግቦች ምንድን ናቸው? በንባብ?
- ልጄ በሂሳብ ክፍል አፈጻጸሙ እንዴት ነው? በእንግሊዘኛ ቋንቋ አርትስ?
- ልጄ እነዚህን ግቦች ለማሳካት በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ የሚያስፈልገው ተጨማሪ ድጋፍ ምንድን ነው?
- በእርስዎ ምልከታ ላይ በመመስረት፣ ልጄ በደምብ የሚሰራው ምንድን ነው? ለልጄ አንዳንድ የእድገት ዘርፎች ምንድን ናቸው?